#ፓፒዮ

•

ካየን የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት። እስርቤቱ ፀባይ ማረሚያ ከሚለው ይልቅ ሕይወት ማሰቃያ ፣ ሕይወት ማጥፊያ ቢባል ትክክለኛ ግጣሙን ያገኛል። ግዜው ደግሞ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መዳረሻ በመሆኑ የእስርቤቶቹ አያያዝ ሰውነትን ያዋረደ ነበረ። በአሰቃቂ ማሰቃያ ቅጣቶች የተሞላ በመሆኑ እንኳን ነፃ ስለመውጣ ማሰብ ቀርቶ ራስን ማጥፋት የሚያበረታቱ ናቸው። ወደ እዛ የገባ ሰው በህይወት እወጣለው ሳይሆን በቅርቡ እሞታለው ብሎ ቢያስብ አያስደንቅም።

አንድ ወደ ሃያ አምስት ዓመት የሚሆነው ወጣት ባላጠፋው ወንጀል ሰው ገድላሃል ተብሎ የዕድሜ ልክ ብይን ይጣልበትና ወደ አሰቃቂው ዞብጥያ ይወርዳል። ሰውዬው በእርግጥ ከመጀመሪያው የእስር ቤቱን ደጅ ከረገጠበት ቀን ጀምሮ ስለማምለጥ ያስባል፣ ያቅዳል፣ ይሞክራል። ከታሰረባቸው የተለያዩ አሰቃቂ እስርቤቶች በማምለጥም ተሳክቶለታል። ከመሞከር አንድም ቀን ቦዝኖ አያውቅም። ሁሌም እንደሞከረ ነው። ብልህና ጠንቃቃ በመሆኑ ድርጊቶቹን በስሜት ሳይሆን በእውቀት ይመራቸዋል። ዕውቀት ነፃ ያወጣል እንዲሉ ከግዞት እስር ቤቶቹ ነፃ ወጥቷል።

ፓፒዮ ወይም በቅፅል ስሙ ቢራቢሮው እንደሚለን ከሆነ "ሕይወት እስካለ ድረስ ምንጊዜም ተስፋ አለ" (ገጽ 343)። ሰውዬው ያለገደብ ተስፋን የተሞላ ሰው በመሆኑ ተስፋ መቁረጥ ሚባለውን ሐረግ ፈፅሞ አያውቀውም ወይም የሱ መዝገበ ቃላት ውስጥ የለም።

ምህረት (ዶ/ር) "በዓለም ላይ ያሉ እሰር ቤቶችን ከሞሉና አሰቃቂ ወንጀሎችን የፈጸሙ እስረኞች አብዛኞቹ የተዛባ ስብዕናና የተበላሸ ልጅነትን ያሳለፉ ናቸው" ሲል በሌላ ሰው መጻሕፉ ይነግረናል (ገጽ 352)። ስለዚህ በማረሚያ ቤቶች የሚጠፈነጉ ታሳሪዮች የስብዕና መዛባት ያጋጠማቸው ናቸው። አሁን ስለስብዕና በሰፊው አንዘረዝረውም። ግን ስብዕና እንደማንኛውም የሰውነት ክፍሎች ይታመማል። ስብዕና የብዙ ነገር ውጤት ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ ግን ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ጓደኛ፣ አከባቢ...ወዘት ተፅኖ ያሳድርበታል። ህፃናት ገና በልጅነት በጤናማ ስብዕና ተቀርፀው እንዲታነፁ የሁሉም ሰው ኃላፊነት ነው። እና በእስር ቤቶች ሰው የገደሉ፣ እስከነነፍሱ የቀበሩ፣ አስገድዶ የደፈሩ፣ በቁም ያቃጠሉ...ወዘተ ታሳሪዎች በሞሉበት ውስጥ ሕይወት ርካሽ ነች። ነፍስ መጠፋፋት ምንም ማለት አይደለም። ግን ሕይወትህ እንዳይጠፋ ዋነኛው መሳሪያ ጉልበትና ተፈሪነት እንደሆነ ከፓፒዮ ስብዕና እንረዳለን።

በእርግጥ ፓፒዮ እንደሚለን "ሰው ነኝ ብሎ የሚያስብ ማንም ሰው እንደዚያ ያለው ሙያ ላይ አይሰማራም" (ገጽ 276)። እናም ታሳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ በአሳቃቂ እስር ቤት ያሉት ጠባቂዎችም ጭምር በተነፃፃሪ ሁኔታ ማንነታቸው የላሸቀ፣ የዘቀጠ ነው። የተቀጠሩትም ታሳሪዎችን ሊያሰቃዩ ነው። በሰው ስቃይ ይረካሉ። እኔ ግን የሚደንቀኝ ሰውን በማሰቃየት የሚገኘው እንጀራ እንዴት ሊዋጥ ይቻለዋል? በረከቱስ ቢሆን?

እንደገና ደግሞ "ሰዎች አንድ መጋረጃ በሁለት ቡድን ይከፍላቸዋል። በአንደኛው ወገን ፍፁም ሕይወት የሌላቸው በድንና የማይንቀሳቀሱ የቢሮክራሲን ስልጣን በመጨበጣቸው ሰውን ለማሰቃየት በሙሉ ፍላጎት የተጠመዱ ይኖራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ እኔና የመሳሰሉ ምናልባት ወንጀል ፈጽማችኋል ተብለው ግን በቅጣታቸው መነሻ በሚደርስባቸው ስቃይ ሐዘንን፣ ርህራሄን፣ መስዋትነትን፣ ጨዋነትንና ልበ ሙሉነትን የመሰሉ ምግባሮችን የሚማሩ ሰዎች ይኖራሉ" (ገጽ 276) በማለት በታሳሪዎችና በጠባቂዎች መካከል ያለውን የሰውነት ልክ ለማነፃፀር ይሞክራል። ጠባቂዎቹ የሞራል ልዕልናቸው ስለተንኮታኮተ ከአንዳንድ ታሳሪዎች ጋር በፍፁም ተቃራኒ እንደሆኑ ይነግረናል። በተቃራኒው ደግሞ ታሳሪዎች በዚህ አሰቃቂ ወንጀሎች በሚፈፀምበት ወህኒ ቤት የሰው መገለጫን ተምረው እንደሚወጡ እና ለሀገር መልካም ዜጋ መሆን እንደሚችሉ ይገልፅልናል። እናም ታሳሪዎችን ልናግዛቸው እንደሚገባ ያሳስበናል።

የፓፒዮ ትጥቅ ተስፋ ነው። ተስፋ የነፍስ ምግብ ነው። ይሄም የሚያስረዳን ተስፋን ያነገበን ሰው ማሸነፍ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ነው። እናም ከፓፒዮ የምንማረው ቁልፍ ትምህርት በዓለም ላይ ስንኖር ፈፅሞ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብን ነው። ተስፋ የሰው ልጅ እስትንፋስ ነው።

የፓፒዮን ተስፈኝነት ከእስር ቤት ዓምድ ወደ ሌላ ሕይወት ስኬት ለማምጣት ሞከርኩኝ። በየትኛውም የስራ ዘርፍ ፓፒዮ ቢሰማራ ስኬታማ የመሆን አቅም አለው። ም/ክ ተስፋ አይቆርጥም፣ ደጋግሞ ይሞክራል። አስራ ሶስት ዓመታትን ከግዞት ስለማምለጥ ያሳለፈውን ጊዜ በፈጠራ ወይም በቢዝነስ ስራ ላይ ያዋለው ቢሆን ኖሮ በሌላ የሕይወት ምዕራፍ ስሙን በደማቅ በማፃፍ ትውልድ በዘከረው ነበር።

እናም መቼም ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም። ተስፋ የቆረጠ ሰው ከመሞቱ በፊት ቀድሞ በቁሙ ደይሟል አይደል የሚባለው።

#ቸር_ጊዜ!

•

#በአንተነህ

#ቅዳሜ ሰኔ ፲፭ ቀን ፳፻፲፩